# ክፍት የሥራ መደብ ማስታወቂያ

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ እና ዩኒቨርሲቲውን በምክትል ፕሬዝዳንትነት ለመምራት ፍላጎትና ብቃት ያላቸውን ተወዳዳሪዎች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የአመራርና የአስተዳዳር ኃላፊዎችን ምርጫ እና ሹመት/ምደባ ለመደንገግ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 002/2011 መሠረት አወዳድሮ የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዝዳንቶች አድርጎ መሰየም ይፈልጋል፡፡

የሥራው መደብ፡- ምክትል ፕሬዝዳንት

ብዛት፡- 2 (ሁለት)፡ (የቢዝነስና ልማት ምክትል ፕሬዝዳንት እና የአስተዳደርና የተማሪዎች ጉዳይ ምክትል ፕሬዝዳንት)

ተፈላጊ ችሎታ

የትምህርት ደረጃ፡- ሶስተኛ ዲግሪ /PhD/፣ ወይም ሁለተኛ ዲግሪ (Master Degree) የትምህርት ዝግጅት ያለው እና ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰር ማዕረግ ያለው/ያላት፣

የሥራ ልምድ፡- በከፍተኛ ትምህርት ተቋም በተለያዩ ደረጃዎች በአመራርነት ቢያንስ የሶስት አመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም ከዚህ ውጪ ባለ መስክ በከፍተኛ አመራርነት የተረጋገጠ የስራ ልምድ ያለው/ያላት፣ እንዲሁም በማስተማርና በምርምር ቢያንስ ስድስት አመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት፡

የዘርፍ ስትራቴጂክ እቅድ፡- የዘርፉን /የስራ መደቡን/ ዋና ተግባር ለማሳደግና ለማሻሻል ስለሚከተለው/ስለምትከተለው ስልት ከ5 ገጽ ያልበለጠ በአማርኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ስትራቴጂክ እቅድ የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ እና የሴኔት አባላት ባሉበት በአካል ማቅረብ የሚችል/የምትችል፡፡

ፆታ፡ አይለይም፤ ሴት አመልካቾች ይበረታታሉ፣

ተፈላጊ ክህሎቶች፡-

የአመራር ክህሎት፡- የዘርፉን የሰው ሃይል፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሃብቶች በማስተባበር ለመምራት የሚያስችል የአመራር ክህሎት ያለው/ያላት፣

አዳዲስ አሰራሮችን የመፍጠርና ለውጥ የማምጣት ክህሎት ያለዉ /ያላት፣

የአሰራር ስልቶችን የመቀየስ፣ የማመንጨትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም ያለው/ያላት፣

የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የተግባቦት ክህሎት ያለው/ያላት፣

ተፈላጊ ስነ-ምግባር፡- አመልካቾች ከስነ-ምግባር ጉድለቶች የጸዱ፣ በመልካም ባህሪያቸው፣ በስራ አከባሪነታቸው የተመሰከረላቸውና ለሌሎች አርአያ የሆኑ፣ ተግባብተው መስራት የሚችሉ እና ለሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ በተገቢው ጊዜ የሚሰጡ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

የስራ ዘመን፡- በውድድሩ የላቀ ውጤት በማምጣት የሚመረጡት አመልካቾች በምክትል ፕሬዚዳንትነት ለአራት ዓመታት የሚሾሙ ሲሆን የስራ አፈጻጸማቸው ታይቶ የስራ ዘመናቸው ለአንድ ተጨማሪ የስራ ዘመን ሊራዘም ይችላል፡፡

ደመወዝና ጥቅማጥቅም፡-በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የደመወዝ፣ የደረጃና ተያያዥነት ባላቸው ህጎችና ደንቦች መሰረት

የማመልከቻ ጊዜ፡- አመልካቾች ሙሉ መረጃዎቻቸውን ማለትም የሚወዳደሩበትን የኃላፊነት ቦታ የሚገልፅ የማመልከቻ ደብዳቤ፣ የትምህርት ማስረጃ፣ የስራ ልምድ ማስረጃ፣ CV፣ እና ሌሎች ለዚህ ውድድር ይጠቅማል የሚሏቸውን መረጃዎች ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ፣ እንዲሁም አጭር ፕሮፖዛል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

የማመልከቻ ቦታ፡- እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ህንጻ ቁጥር 02 ሶስተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 309 በአካል ቀርበው ማስገባት ወይም ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀው ኢሜል አድራሻ vicepresident@inu.edu.et መላክ ይችላሉ፡፡

ለበለጠ መረጃ፡- በ 0918701855 ወይም 0913465212 ስልክ ቁጥሮች ደውሎ ማነጋገር ይቻላል፡፡

#የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ስራ አመራር ቦርድ